# የACPS Express 3/24/2023: የማርች (March)፣ ተማሪን እና ሠራተኛን - እውቅና-መስጠት

## የማርች (March)፣ ተማሪን እና ሠራተኛን - እውቅና-መስጠት




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች እና ሠራተኞች ውጤታማነት፤ በ‘ACPS Express’ በራሪ-ወረቀት/newsletter ላይ በየወሩ የሚገለጹ-ይሆናሉ። በዚህ-ወር እውቅናን-በመስጫው ጽሁፍ-ላይ፤ ጥቂቶቹ የክፍሉ/division ውጤታማነቶች ብቻ ተካትተዋል።

## የ‘ACHS Debate Team’ ወቅቱ/Seasonን - በስኬታማነት አጠናቋል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የ‘Debate Team’፤ በሊጋቸው ውስጥ የወቅቱን ውድድር ያጠናቀቁ እና ለዓመቱ አጠቃላይ ነጥቦች የሆነውን - የሦስተኛ ደረጃ ዋንጫቸውን ወስደዋል። አለና ኩፐር (Alena Cooper) እና ጆን ብሮክ (John Brock) በብሄራዊ ውድድር ላይ ለመወዳደር- እንዲሁም አፖሎ ዘብረ (Apollo Zebre) እና ሶፊአ ብራሲንግተወት (Sophia Bassingthwaite) ደግሞ በጁኒየር ቫርሲቲ ክፍል (junior varsity division)፣ ለሜትሮፋይናል ውድድር (metrofinals tournament) ተወዳድረዋል።

የ‘ACHS’ የክርክር ቡድን (debate team)፤ በዋሽንግተን-አርሊንግተን ካቶሊክ ፎረንዚክ ሊግ (Washington-Arlington Catholic Forensic League) ውስጥ፣ በአካባቢው ለሚገኙ ሁሉም የህዝብ እና የግል ትምህርት ቤቶች ክፍል በሆነው ሊግ/league ውስጥ ይወዳደራል። ተማሪዎቹ፤ አሜሪካ በ‘North Atlantic Treaty Organization (NATO)’ ውስጥ ያላትን የሴኩሪቲ ትብብርን - የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ/artificial intelligence፣ ባዮቴክኖሎጂ/biotechnology እና/ወይም ሳይበርሴኩሪቲ/cybersecurity - ማሳደግ-አለባት ወይንስ የለባትም በሚል የሚዳስሱ ይሆናል። በአጠቃላይ ወቅቱ/season ውስጥ፣ የክርክር ቡድኑ - በሁለቱም ጎን በኩል ያሉትን መከራከርያ-ነጥቦች ላይ መከራከር የተማሩበት ሲሆን፤ የምርምር እና አመዛዝኖ የማዘብ ችሎታቸው እየገነቡ ባሉበት-ጊዜ፣ ከዚሁ-ጎን ለጎን የእነዚህን ዓይነት ጥያቄዎች ውስብስብነት ለመመልከት ያስቻላቸው ነበር።

## የ‘Stellar ACHS Satellite’ ተማሪ - የቅድመ ምርቃት ዓላማን (Early Graduation Mission) ስኬታማ-አድርጓል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የሳተላይት ካምፓስ (Satellite Campus) ተማሪ አይዚሃ ሮቢንሰን (Isaiah Robinson) - በቅድሚያ ለመመለቅ እይታውን በማስተካከሉ እናም የሚያደርገው-ነው። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማውን ከ11ኛ ክፍል በኋላ ከማግኘቱ በተጨማሪ፣ በበርካታ ኮሌጆች ውስጥ ተቀባይነትንም አግኝቷል። ሜሪማውንት ዩኒቨርስቲ (Marymount University)፣ ለሮቢንሰን (Robinson) - የአራት-ዓመት ስኮላርሽፕን ሰጥቶታል።

“አይዚሃ (Isaiah)፣ በACHS ሳተላይት (Satellite) ውስጥ - ኮርሶቹን ለማጠናቀቅ ጠንክሮ-የሰራ በመሆኑ - በቅድሚያ ለመመረቅ ያለውን ግቡን ለማሳካት አስችሎታል፣” ብለዋል የሳተላይት ካምፓስ (Satellite Campus) አስተዳደር ፍሬደሪካ ኤል ስሚዝ (Fredericka L. Smith)። “አማራጭነት ባለው መንገድ ወደ ምርቃት ለመሳትፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች - አዎንታዊ የሆነ አስተዋጽዖ በፕሮግራማችን-ላይ በማምጣት - ምሳሌ ሊሆን የቻለ ነው። በአይዚሃ (Isaiah) ስኬታማነት በጣም ኮርቼበታለሁ።”

ሮቢንሰን (Robinson) - ንግድ/businessን እንደ የትምህርት ምርጫው-ከግምት ውስጥ እያስገባ-ይገኛል።

## የACHS ሲኒየር/Senior፣ ወደ ብሄራዊ ሜሪት ስኮላርሽፕ ማጠቃለያ (National Merit Scholarship Finals) አልፏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ሲኒየር/senior ናታኔኤል በርክሄድ (Nathaniel Burkhead) - በቅርቡ የ‘Certificate of Merit’ን ያገኘ እና በብሄራዊ ሜሪት ስኮላርሽፕ ፕሮግራም (National Merit Scholarship Program) ወደ መጨረሻ-ተወዳዳሪነት አልፏል። በርክሄድ (Burkhead)፣ በፊዚክስ እና በሂሳብ ግንኙነት-ባለው የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ (post-secondary) ለመቀጠል ዕቅድ አለው።

በግምት ወደ 7,250 ለሚጠጋው የዚህ-ዓመት የብሄራዊ ሜሪት ስኮላርሽፖች (National Merit Scholarships)፤ ከ15,000 በላይ ለመጨረሻ-ውድድር የደረሱን ከግምት-ውስጥ ያስገባ አድርጓል። አሸናፊዎቹን፤ በአራት አገር-አቀፍ ጋዜጣዊ-መግለጫዎችን - በኤፕሪል (April) ወር መጀመሪያ ላይ ጀምሮ የሚያሳውቅ፣ እና በጁላይ (July) ወር ውስጥ ይጠናቀቃል።

## የጆን አዳምስ (John Adams) አስተማሪ - ለ'Prestigious Military Scholarship' ተመርጠዋል



ሄሉ ፓድጌት (Haley Padgett)፣ በጆን አዳምስ (John Adams) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የአምስተኛ ክፍል አስተማሪ እና በውትድርና/military ሚስት የሆኑት፤ በስመጥሩ የቲልማ ስኮላርስፖች (Tillman Scholars) ፕሮግራም - ከPat Tillman Foundation ተመርጠዋል። ይህ ፕሮግራም እገዛ-የሚያደርገው፤ በሃገራችን የውትድርና አገልግሎት አባላቶች፣ ቬተርናን እና የውትድርና ባል/ሚስት የሆኑትን፤ በምትህርታቸው ላይ እና በሕይወታቸው ሙሉ በአማራርነት ዕድገት እንዲያመጡ - በሁለቱም በአካባቢው እና በዓለም-አቀፍ ደረጃ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ የሚያበቃቸው ነው።

"በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ውስጥ በየቀኑ የምንሰራውን ወሳኝ እና ጠቃሚ-የሆነ ስራ ለማሳየት በመቻሌ ከፍተኛ ኩራት-ይሰማኛል፤" ፓድጌት (Padgett) በማለት-ተናግረዋል። "ይህን ዕድል፤ ለተማሪዎቻችን የተሻለ ውጤትን በማምጣት እንዲቀጥሉ ለመርዳት - በአዕምሮ ጤና እና ጤናማነታቸው ላይ እገዛን-በመስጠት በመስራት-ለመጠቀም አቅዳለሁ።"

የፓድጌት (Padgett) የረጅም-ጊዜ ዕቅዶች የሆኑት፤ ከትውልድ-ወደትውልድ ሲሸጋገር ለመጣው ድህነት እና ጥቃት እየተቸገሩ ያሉትን ማህበረሰቦችን - እንዲሁም በቅርቡ የመጡ ስደተኞች እና ጥገኝነት-ጠያቂዎችን - የማማከር/counseling አገልግሎቶችን በማሳደግ- የማግኘት አቅም-እንዲኖራቸው ማድረግን ያካትታል። ስለ Padgett's scholarship በኦንላይን-ላይ የበለጠ እወቁ።

## የACPS የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች - በቨርጅኒያ የታሪክ ቀን (Virginia History Day) ውድድር - ወደ ቀጣዩ-ደረጃ አልፈዋል



አርባ-ሰባት የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች፤ በቨርጅኒያ ታሪክ ቀን የዲስትሪክት 5 ውድድር (Virginia History Day District 5 Competition) - በማርች (March) 4 ቀን 2023 ላይ ተወዳድረዋል። በዝርዝሩ ያሉት ተማሪዎች፤ ወደ ስቴት-አቀፍ ውድድር በኤፕሪል (April 29-30, 2023 - ውድድር ላይ፣ ፕሮጀክታቸውን ከሰራው አድማጭ-ተመልካች ጋር እንዲያጋሩ አልፈው-ነበር።

አሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School):

- አና ብሮንዌን ተርኒ (Anna Bronwyn Turney): የመጀመሪያ ደረጃ ቦታ፣ የግል ወረቀት (individual paper): “The Oxford English Dictionary: A Landmark in Language.”
- ቪዮሌት ፕሌኒ (Violet Planey): የሦስተኛ ደረጃ ቦታ፣ የግል ዶኩሜንተሪ (individual documentary): “Earth's Greatest Hits: Voyager and the Golden Record.”

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት:

- ሉኒቫ ዴሳር (Luniva Desar): የሁለተኛ-ደረጃ ቦታ፣ የግል ድህረ-ገጽ (individual website): “The Lewis and Clark Expedition: Exploring a New Frontier.”
- ሊሊ ረግለር (Lily Regler): የሦስተኛ ደረጃ ቦታ፣ የግል ዶኩሜንተሪ (individual documentary): “Battle of Bull Run.”

ጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት:

- ሆፕ ኪብር (Hope Keber) እና ፔጅ ቮግል (Page Vogel): የመጀመሪያ ደረጃ ቦታ፣ የቡድን ዝግጅት-አቀራረብ (group performance): “The Match Girls Strike of 1888.”
- ጄነቪቭ ዴልተን (Genevieve Dalton): የሁለተኛ ደረጃ ቦታ፣ የግል የዝግጅት-አቀራረብ (individual performance): “Educated Necessary Independent Advanced Computers and the ENIAC: The Women of the World's First Modern Computer.”
- አሊስ ሆሎራን (Alice Halloran) እና ክሌር ዋልሽ (Claire Walsh): የሁለተኛ ደረጃ ቦታ፣ የቡድን ዝግጅት-አቀራረብ (group performance): “A Comfortable Frontier; Coco Chanel’s Fashion Revolution.”
- ሶፊያ ዌላን (Sophie Whelan): የሁለተኛ ደረጃ ቦታ፣ የግል ማሳያ (individual exhibit): “Samuel Tucker's 1939 Alexandria Library Sit-in.”

የቨርጂኒያ የታሪክ ቀን - ከስቴቱ/state ጋር ትብብር ያደረገ የብሄራዊ የታሪክ ቀን ሲሆን፤ በፕሮጀክት-ላይ መሠረት ያደረጉ የመማር ፕሮግራምን ከ4-12 ክፍሎች ውስጥ ለሆኑ ተማሪዎች የሚቀርብበት-ነው። ይህን ባለብዙ-ዘርፍ የምርምር ፕሮጀክት - ተማሪዎች በታሪካዊ አስተሳሰብ እንዲጎለብቱ እና የማንበብና መፃፍ ችሎታቸውን በታሪክ ጥናት ላይ በመሳተፍ - አስፈላጊ እና አስደሳች-ለማድረግ የሚረዳቸው-ነው።

## የ‘ACHS’ ተማሪዎች እና ሠራተኞች - ከዓለም-አቀፍ ስራ-ፈጣሪነት ድርጅት (International Entrepreneurship Organization) ክብርን-አግኝተዋል




ሰላሳ-ዘጠኝ የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች፣ በ‘Distributive Education Clubs of America (DECA)’ የስቴት አመራርነት ኮንፈረንስ - በሆነው ውስጥ በቨርጂኒያ ቢች (Virginia Beach)/ Virginia፤ በዚህ ወር ውስጥ፣ ተወዳድረዋል። አስር ተማሪዎች ማዕረጋቸውን ያገኙ እና ስምንት ለዓለም-አቀፍ የስራ-መስክ እድገት ኮንፈረንስ - በኦርላንዶ ፍሎሪዳ (Orlando, Florida) - በኤፕሪል (April) ወር ውስጥ ለሚካሄደው - ብቁነታቸውን አረጋግጠዋል።

የሚከተሉት ተማሪዎች የስቴት-ለመጨረሻ የደረሱ/state finalists ነበሩ:

- ጃዝሚን ቤርሊ (Jasmine Bailey) እና አዴር ጋብሪኤል (Adair Gabriel)፤ ‘Buying and Merchandising Team Decision Making’።

- አሌክስ ሲርሞ (Alex Cirmo)፣ ‘Entrepreneurship Series’።
- አዴር ጋብሪኤል (Adair Gabriel)፤ ‘Buying and Merchandising Team Decision Making’።
- ዊሊያ ራይሊ (William Reilly) እና ካሌብ ዋርድ (Caleb Ward)፤ ‘Business Law and Ethics Team Decision Making’።
- ሳዳ ሰማን (Sada Seman)፤ ‘Principles of Finance Exam’።
- ሴፍ ሻንናግ (Saif Shannag)፤ ‘Principles of Hospitality and Tourism’።

የሚከተሉት ተማሪዎች፤ በፍሎሪዳ/Florida - በዓለም-አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ የሚወዳደሩ ናቸው:

- ጃዝሚን ቤርሊ (Jasmine Bailey) እና አዴር ጋብሪኤል (Adair Gabriel)፤ ‘Buying and Merchandising Team Decision Making’።
- አኒቤል ዳውሰን (Anibel Dawson)፤ ‘School Based Enterprise — Titan School Store’።
- ማሊ ሂል (Andrea Hill)፤ ‘School Based Enterprise — Titan School Store’።
- ዊሊያ ራይሊ (William Reilly) እና ካሌብ ዋርድ (Caleb Ward)፤ ‘Business Law and Ethics Team Decision Making’።
- ጄከብ ሳንቼዝ (Jacob Sanchez)፤ ‘School Based Enterprise — Titan School Store’።
- ሳዳ ሰማን (Sada Seman)፤ ‘#2 in the State of Virginia for the DECA Principles of Finance Individual Series Role Play Event’።

የፋሽን የግብይት አስተማሪ - ተሬሳ ሻቬስ (Teresa Chavis) እና ካትሪን ልዊስ (Catherine Lewis)፤ በባለ-ሁለት ጥምረት ምዝገባ ትምህርት-ሰጪ/ተጓዳኝ ፕሮፌሰር - ለ‘Entrepreneurship I and Advanced Entrepreneurship II’፤ የ‘Outstanding DECA Advisor’ ሽልማት - ተሰጥቷቸው-ነበር።

DECA - በተጨማሪም እውቅናን-ሰጥቶ የነበረ፣ የ‘ACHS Titan School Store’ን እንደ የላቀ-ደረጃ ያለው በትምህርት ቤት መሠረት ያደረገ ድርጅት አድርጎ-እውቅና-ሰጥቷል። ከ461 በትምህርት ቤት መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች መካከል የ‘gold level re-certification’ን ለ2022-23 የትምህርት ዓመት ያገኘ፣ እና በዓለም-አቀፍ ኮንፈረንሱም ላይ እውቅናን ያገኛል።

DECA - በዓለም-ዙሪያ - በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚያገለግል ድርጅት ነው። ከ224,000 ተማሪ አባላቶች በላይ፤ DECA - ብቅ-እያሉ ለሚመቱ መሪዎች፣ እና ስራ-ፈጣሪዎች (entrepreneurs) - በግብይት/marketing፣ ፋይናንስ፣ እንግዳ-አቀባበል/hospitality እና አስተዳደር/management ውስጥ - ለስራ-መስኮችን የሚያዘጋጅ-ነው። ተጨማሪ መረጃዎች፤ በ[Virginia DECA State Leadership Conference Top 20 list] ላይ መገኘት ይችላል።

## የ‘ACPS’ ተማሪዎች፣ በክልላዊ የሣይንስ ትዕይንት ላይ እውቅናን-አግኝተዋል




በማርች (March) 4 ቀን 2023 ላይ በተካሄደው የ‘2023 Northern Virginia Regional Science and Engineering’ ትዕይንት ላይ፣ ከ70 በላይ የሚሆኑ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች ተካፍለው-ነበር። ዘጠኝ የ‘ACPS’ ተማሪዎች፤ የመጀመሪያ-ደረጃ ቦታ ያለውን ክብር-አግኝተዋል። በተጨማሪም፤ 14 የሁለተኛ ደረጃ-ቦታ ያገኙ፤ 21 የሦስተኛ ደረጃ-ቦታን ያገኙ እና 19 በክብር-የተጠሩ ነበሩ።

“ተማሪዎችን ለዚህ ዓመት የሣይንስ ትዕይንት ወቅት ሙሉ ለረዳችሁ ለሁሉም የሣይንስ አስተማሪዎች ምስጋናችንን እናቀርባለን፤” ብለዋል የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የሣይንስ ትዕይንት መሪ - ኢሪን ስትሪፐለ-ባርከር (Erin Striple-Barker)። “ለተማሪዎቻችን ያደረጋችሁት ጠንካራ-ስራ እና ትጋት በእውነት-የሚመሰገን-ነው።”

አራት የጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ ለ‘2023 Thermo Fisher Junior Innovators Challenge’ ስያሜን-አግኝተዋል። እነርሱም፤ ቶማስ በርክስ (Thomas Burks)፣ ካርስቲን ትሬጋስኪስ ጎርዶን (Karsten Tregaskis Gordon)፣ አሜሊአ ሃርትሌት (Amelia Hazlett) እና ሲኤና ሌስተር (Siena Lester) ናቸው።

በአምስት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሰሩት - ሦስት ፕሮጀክቶች፤ ወደ የ‘2023 Virginia State Science and Engineering’ ትዕይንት ላይ እንዲያፍልፉ ሃሳብ-ቀርቧል። እነርሱም፤ ከACHS-ሚኔ ሃዋርድ ካምፓስ (Minnie Howard Campus) – አሪአና እስፒሪቱ (Arianna Espiritu) እና ጋርሴ ሄቲንገር (Grace Hettinger) እና፣ ከACHS፣ ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) – ብሪጂት ባረን (Bridget Baron)፣ ጁሊያ ሳየር (Julia Sayre) እና ሚእሩ ዊን (Mary Winn) ናቸው። ይህ ዝግጅት- በአካል-ተገኝቶ - ከኤፕሪል (April) 14-15 ቀን 2023፤ በኦልድ ዶሚኒየን ዩኒቨርስቲ (Old Dominion University) የሚካሄድ ይሆናል።

“በፈጠራዊ-አስተሳሰብ፣ በፈጠራዊነት እና በACPS ተማሪዎች ትጉህነት - ከፍተኛ-አድናቆት አድሮብናል። እንኳን-ደስ አላችሁ፤ እና በዚህ ዓመት የ‘Northern Virginia Regional Science and Engineering Fair’ ላይ ለተሳተፋችሁ ሁሉ ምስጋናችንን-እናቀርባለን፤” ብለዋል የ‘STEM’ አስተባባሪ እና የመጀመሪያ ደረጃ የሂሳብ የትምህርት-አሰጣጥ ባለሞያተኛ ጁሊአ ኑውፈር (Julia Neufer)።

## የ‘ACHS’ የትግል-ተወዳዳሪዎች/Wrestlers፤ በ‘VHSL State Championship’ ላይ ተወዳድረዋል



ሦስት የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የትግል-ተወዳዳሪዎች/wrestlers፤ በቨርጂኒያ ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ሊግ የስቴት ሻምፒዮና (Virginia High School League State Championships) ላይ በፌብሩዋሪ (February) ውስጥ ተወዳድረዋል። ካልቪን ዌደርመር (Calvin Weidemer) በውድድሩ የሦስተኛ ደረጃ ቦታን ያገኘ እና ባሰም ስሊቲ (Bassem Sliti) እና ጁኤልዝ ፒተርስ (Juelz Peters) ተጋጣሚዎቻቸውን ሁለቱም አሸንፈዋል።

የትግል-ዋና አሰልጣኝ በሆኑት በክሪስ ማርሻል (Chris Marshall) አመራርነት-ስር ሆነው፤ ሁሉ ሦስት የትግል ተወዳዳሪዎች/wrestlers - ይህን-ውጤታማነትን ለማግኘት-ችለዋል። ዌደርመር (ዌደርመር)፣ የትግል-ውድድሩን/wrestling - በዋሽንግተን እና በሊ ዩኒቨርሲቲ (Washington and Lee University) ውስጥ በሚቀጥለው ዓመት ይቀጥላል። ብሉፊልድ ዩኒቨርስቲ (Bluefield University) እና ሜሪማውንት ዩኒቨርስቲ (Marymount University) - ሁለቱም ዩኒቨርስቲዎች - በስሊቲ (Sliti) ላይ ፍላጎታቸውን አሳይተዋል። ፒተርስ (Peters) ሶፎሞር/sophomore የሆነ፣ እና በሚቀጥለው ዓመት ወደ ቡድኑ በሚመለስ ጊዜ አብሮ-መስራትን ለመቀጠል ደስተኛ-መሆናቸውን ማርሻል (Marshall) ገልጸዋል።

## ነፃ በጤናማነት - የቅድመ-ትምህርት ቤትን መጀመር ትዕይንት (Fair)፣ ቤተሰቦች ለ‘VPI’ ምዝገባ ዝግጁ-እንዲሆኑ ይረዳቸዋል




ሁሉም የአራት-ዓመት ልጆችን በዚህ በልግ (fall) ውስጥ በAlexandria Virginia Preschool Initiative (VPI) ፕሮግራሞች ውስጥ ለሚያስመዘግቡ ቤተሰቦች በሙሉ፤ ወደ አሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ-ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) የቅድመ-ትምህርት ቤት ጤና የመረጃ-ምንጮች ዝግጅት ላይ - ሰኞ፣ ኤፕሪል (April) 10 ቀን 2023 ላይ እንዲካፈሉ ተጋብዘዋል። የACPS ትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች - ከቅድመ-ልጅነት ፕሮግራም (Early Childhood Program) ጋር በመተባበር፤ በፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ - (1701 N. Beauregard Street)፣ ከ9 a.m.-12 p.m. ድረስ የ"Healthy Start Preschool Fair"ን አዘጋጅቷል። ዝግጅቱ፤ ነፃ የትምህርት ቤት ህክምና/school physicals፣ ክትባቶች/immunizations እና ለቅድመ-ትምህርት ቤት ተማሪዎች ምዝገባ የሚያስፈልጉትን የጤና መስፈርቶችን - የሚሰጥ-ይሆናል። ጠቃሚ-የሆኑ - ለቅድመ-ትምህርት ቤት ቤተሰቦች የማህበረሰብ የመገኛ ምንጮች (resources) የሚሰጡ-መረጃዎችም የሚኖሩ-ይሆናል።

ምዝገባ ያስፈልጋል። ለመመዝገብ፣ ወይም ስለዝግጅቱ ማንኛውንም ጥያቄዎች ለመጠየቅ፤ እባካችሁ በ vpiearlychildhood@acps.k12.va.us ኢሜል አድርጉ። በራሪ-ማስታወቂያዎች/Flyers፤ በ እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ ዳሪ፣ አማርኛ እና አረብኛ ቋንቋዎች መገኘት-ይችላል።

## የ‘Youth Art’ ወር እና ‘National Music’ - በትምህርት ቤቶቻችን ወር: PTAC ያዘጋጀው - “Reflections” የስነ-ጥበብ ውድድር (Art Contest)



የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (PTAC) የ‘Reflections’ ፕሮግራም፤ የ‘Youth Art’ ወር እና ‘National Music’ - በትምህርት ቤቶቻችን ወር - ህይወት-እንዲያገኝ አድርጓል። በተማሪዎች በተመረጠው “show your voice” ገጽታ/theme ላይ ምላሽ-በመስጠት፤ ከ14 የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) የተዘጋጁ - በሁሉም የተዘጋጁት ምድቦች ውስጥ ከዋና/ኦሪጂናል የሆኑ የስነጥበብ/art ስራዎች ውስጥ 129 ተማሪዎች ዝግጅታቸውን

አቅርበዋል። እነዚህ የዲስፕሊኖች-ዓይነቶች/disciplines ያካተቱት፤ የኮሪኦግራፊ ዳንስ/dance choreography፣ የፊልም ስራዎች፣ በስነ-ጽሁፍ፣ ሙዚቃ ቅንብር፣ በፎተግራፍ-ስራ፣ በዕይታ ስነጥበባት (visual arts) - አካተዋል።

እነዚህ 52 የመጀመሪያ ደረጃ-ቦታን ያገኙ አሸናፊዎች፣ ከትምህርት ቤቶቹ ወደ PTAC Reflections Contest ተልከው-ነበር። “በእነዚህ በእኛ 17 እጅግ-ግሩም የሆነ ተሰጥዖ ባላቸው ዳንስ-ደናሾች፣ ፀሃፊዎች፣ አቀናባሪዎች፣ ፎተግራፈሮች፣ እና ሰዓሊያኖች የተሰራውን - ወደ ‘Virginia State PTA Reflections Contest’ መግባት-በመቻላቸው ኩራት-ተሰምቶናል፤” ብለዋል የ‘PTAC’ ፕሬዚዳንት - ሚሲ ኤስታብሩክ (Missy Estabrook)።

ሦስት የ‘ACPS’ ተማሪዎች - በስቴት-ደረጃ ክብርን-አግኝተዋል:

- በ‘Intermediate Film Category, Outstanding Interpretation’: ኤንጀል ማንገም (Angel Mangum)፣ ጀፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት።
- በ‘Primary Photography Category, Award of Excellence’: ካልቪን ጌይ ፓርክስ (Calvin Guy Parks)፤ በዳግለስ ማክአርተር (Douglas MacArthur) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት።
- በ‘Primary Visual Arts Category, Award of Excellence’: ኤቨሊን አልቪስ (Evelyn Alves)፣ በቻርልስ ባሬት (Charles Barrett) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት።

“የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል - ‘Reflections’ ፕሮግራም፤ እውቅናን እንዲያገኙ እና ወደ ስነ-ጥበባት/arts እንዲገቡ ዕድሎትን የሚሰጥ ሆኖ፤ የተማሪውን በራስ-መተማመን እና ስኬት በስነጥበብ/arts ውስጥ እና በህይወት-ውስጥ ከፍ-ከፍ አድርጎ የሚያነቃቃ ነው፤” ብለው-ገልጸዋል፣ ኤስታብሩክ (Estabrook)።

## የACPS ቤተሰቦች፤ በ‘AVID Event’ ላይ ለኮሌጅ ስለመሰናዳት ተምረዋል



የ‘The Advancement Via Individual Determination (AVID)’ የቤተሰብ ዝግጅት፤ ቅዳሜ ማርች (March) 18 ቀን 2023 - በይበልጥ-መረጃ ሰጪ ብቻ የነበረው — በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ - ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ አስተማሪዎች፣ አስጠኚዎች/tutors እና ፕሮግራም አስተዳዳሪዎችን ሁሉንም-በአንድነት ያመጣውን ዝግጅት-አዘጋጅቶ ነበር።

ዝግጅቱ የጀመረው የነበረው - ቤተሰቦች ቁርስ እየተመገቡ፤ ስለ ‘AVID’ - እንዴት ተማሪዎች በኮሌጅ እና የስራ-መስክ ዕድሎች እንደሚረዳ፣ ጠንከር-ብሎ በሚሰጠው የከፍተኛ ደረጃ ኮርሶች ውስጥ - ተማሪዎችን ወደ ኮሌጅ ሊያሰናዳ በሚችል እና ገንዘብን ለመቆጠብ የሚወሰዱ አንዳንድ-ትናንሽ እርምጃዎችን አሁን-በማወቅ በኋላ በገንዘብ ምክንያት የሚመጣን-ጭንቀትን ለማስወገድ እንዴት እንደሚረዳ በመማር ተሳትፈው-ነበር።

ልዊስ አለሃንድሮ ሮድሪገዝ (Luis Alejandro Rodriguez) - በACHS ውስጥ ጁኒየር/junior የሆነ፣ የthe school’s AVID program አንዱ-አካል የሆነ ነው።

“AVID - ግሩም-ከሆኑት የተሳተፍኩባቸው ፕሮግራሞች ውስጥ አንዱ-የሆነ እና፣ አስፈላጊ-የሆነ ክፍል ለእኔ-ሆኖልኛል፣” ሮድሪገዝ (Rodriguez) እንዳለው። “ከ‘AVID’ጋር የሚሰሩ አስተማሪዎች ከተማሪዎች ጋር ግንኙነት-የማድረጊያ ግሩም-የሆነ መንገድ አላቸው፣ እና ይህ በእርግጠኛነት — የሚፈልጉት-ነገር ሲኖር የሚያናግሩ-ሰው እንዲኖራቸው የሚረዳቸው፣ እና በእርግጠኛነት በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ዓመቶቼ ውስጥ ረድቶኛል።”

‘AVID’ - የኮሌጅ ዝግጁነት ፕሮግራም ሆኖ በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤት (Alexandria City Public School (ACPS) ውስጥ - ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው - የመካሪ-አገልግሎት (mentoring) እና የኮሌጅ ማግኛ የመረጃ-ምንጮችን፣ የገንዘብ-እርዳታ (financial aid) መረጃዎችን በማግኘት፣ እና ከከፍተኛ-ደረጃ በኋላ ተገቢ-በሆነ ኮሌጅ ውስጥ - የበለጠ ተወዳዳሪነትን ይዞ-ለመገኘት የሚያስፈልጉትን ችሎታዎች ለማዳበር የሚረዳ-ነው። ተማሪዎች የ‘AVID’ እርዳታን - በ‘elective class’ አማካኝነት፣ በመካከለኛ ደረጃ (middle) ትምህርት ቤት ውስጥ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምርቃት ድረስ አግኝተዋል።



“የምናቸርገው ነገር፣ ተማሪዎችን የችሎታዎችን አጠቃላይ ዝግጅትን እና ስልቶችን ለማስተማሪ ሲሆን፣ ይህም በቀለም-ትምህርት ባህሪይ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር-ግን - የራስን መቆጣጠር ስልቶችን እንዲያውቁ፣ ነገሮችን የማቀናበር ችሎታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ፣ ጊዜን-በአግባቡ ለመጠቀም እንዴት እንደሚቻል፣ እና እነዚህ-ችሎታዎች ሁላችንም በህይወታችን የሚያስፈልጉንን ለማሳወቅ ነው፤” ብለዋል ጆዲ ፒተርስ (Jodie Peters) - የ‘AVID’ ዲስትሪክት ዳይሬክተር። “ተማሪዎች በስራ-መስካቸው ውስጥ ምንም እንደሚፈልጉ ማወቅ በጣም ወሳኝ ነው፣ እና ይህን-ማድረጋቸው በስራ-ኃይሉ ውስጥ ምርጫዎች ይኖራቸዋል እና የሚወዱትን ስራ ለመስራት ይችላሉ።”

በቅዳሜው ዝግጅት ላይ የተካሄዱት ሁሉም ውይይቶች፤ በስፓኒሽ፣ ዳሪ፣ አማርኛ፣ እና አረብኛ ቋንቋ - የበለጠ ሁሉም አሳታፊ የሆነ ተሞክሮ ለቤተሰቦች በአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው እንዲያገኙ ለማድረግ - የማስተርጎም-አገልግሎት ተሰጥቶ ነበር።

“ተማሪዎች በእኔ ዙሪያ ሲሆኑ የተመቻቸ ስሜት እንዲኖራቸው ማድረጉ፤ ከእነርሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት የበለጠ ጥልቀት ያለው እንዲያደርገው አድርጎታል፤” ብለው - ሎራ ፈንስ ኩውኞኔስ (Laura Funes Quiñonez) - የዘጠነኛ ክፍል የ‘AVID’ አስጠኚ/tutor - ገልጸዋል። “በቀለም-ትምህርት ብቻ መርዳት ብቻ ሣይሆን፣ ነገር-ግን በየየግል-ሁኔታቸውም ላይ የሚረዳ-ነው።”

አንዳንድ ተማሪዎች እንደ ሚሼል ባራሆና ኢሩቲአ (Michelle Barahona Urrutia) ከኮሌጅ በኋላ - በ‘AVID’ ውስጥ የተማሩትን ችሎታዎች - ማስፈጸም-ችለዋል። ባራሆና ኡሩቲአ (Barahona Urrutia) ክፍሉን በሰባተኛ-ክፍል ውስጥ መውሰንድ - ጀምረው-ነበር።

“የእውኑን-ዓለም ችሎታዎች እንደ ሬዙሜ(resume) መፃፍ፣ ኔትወርክ-ማድረግ እንዴት በስራ-ላይ ማዋል እንደሚቻል ማወቅ — የምሄድበትን ጎዳና እንዳውቅ እና ግቦችን እንዳስቀምጥ እና እነዚህንም ግቦች ለማሳካት መንገዶችን እንድፈልግ ረድቶናል፣” ብላለች። “የ‘AVID ፕሮግራም’ን እወደዋለ።”

ስለ ‘AVID’ በአጠቅላይ ለመማር እና በፕሮግራሙ አማካኝነት ለተማሪዎች ስለሚሰጠው እገዛ-ለማወቅ፤ ድህረ-ገጹን ጎብኙ።

# የተማሪ ዶኩመንታሪ - በአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ ውስጥ የማስታወሻ ፕሮጀክት - ታዋቂ-የሆነ የስቴት ሽልማትን አሸነፈ



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች፤ ለሰብዓዊ ግንኙነቶች እና የሰብዓዊ መብቶች - የማይረሱ-ትዝታዎችን እና አሳዛኝ ተሞክሮዎችን በመዝገብነት የሚያሳየውን - እንደ አሌክሳንድርያ ማህበረሰብ የማስታወሻ ፕሮጀክት (Remembrance Project) - የ'Virginia Education Association Barbara Johns Youth' ሽልማትን አሸንፏል። የ'ACHS' የ'Black Student Union'፣ የቲያትር መምሪያ እና ቴሌቭዥን እና ሚዲያ ዝግጅት መምሪያ፤ የተሰጣቸውን ክብር - በማርች (March) 17 ቀን 2023 ላይ፣ በ'Virginia Education Association's Fitz Turner Commission for Human Relations and Civil Rights' የሽልማት ስነ-ስር ዓት ላይ ተቀብለዋል።

ሽልማቱ-ተገኝቶ የነበረው፤ የACHS ተማሪዎች በትብብር በሰሩት ዶኩሜታሪ/documentary ላይ፣ በአላባማ/Alabama ውስጥ በ'Equal Justice Initiative's National Memorial for Peace and Justice and Legacy Museum' ጉብኝታቸው ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ በማንጸባረቅ ላይ በተሰራው ዶኩሜታሪ ነበር። ይህ የሰብዓዊ መብቶች የጉብኝ-ጉዞ፤ የአሌክሳድርያ የግድያ ሰለባዎች የሆኑት - ጆሴፍ ማክ ኮሪ (Joseph McCoy)ን በ1897 እና ቤንጃሚን ታመስ (Benjamin Thomas)ን በ1899 ህይወታቸውን በምልከታ-ለማንጸባረቅ፤ የ'Remembrance Project' የተሰበሰበውን አፈር (soil collected) ማቅረብን ያካተተ-ነበር። የተማሪዎች የአድቫይዚን እና የዕቅድ ኮሜቴ ቡድኑ የሚያካትተው፤ የACHS አስተማሪዎችን - ሌስሊ ኤ. ጆንስ (Leslie A. Jones)፣ ራአሊም ሻባዝ (RaAlim Shabazz) እና ቪልማ ዘፍራን (Vilma Zefran)፤ እና የቀድሞ የACPS አስተማሪ ቤን ሊየን (Ben Lyon) ያካተተ-ነው።



"ወደ 'Remembrance Project pilgrimage' የሄድኩት - ይህ የመስክ-ጉዞ (field trip) ለተማሪዎቻችን ጥሩ-ተሞክሮ ይሆናቸዋል በሚል-በማሰብ ነው፤" ብለዋል ጆንስ (Jones)። "በዚህ ፒልግረሚጅ/pilgrimage ጉዞ ይሆናል-ብዬ ያልገመትኩት፤ ይህን ያህል ህይወትን የሚቀይር እና የሚያሸጋግር ይሆናል ብዬ-አላልኩም ነበር - ይህም ለተማሪዎቻችን ብቻ ሳይሆን ነገር-ግን ለእያንዳንዳችን እና ለሁላችንም ጭምር-የሚቀይርልን ነው። በጭራሽ-አንድ ዓይነት ሰው እንደማልሆን አውቄአለሁ። ተማሪዎቻችን፤ የተሻለ ትምህርት-ሰጪ፣ የተሻለ ሰብዓዊነት-ያለው፣ እና የተሻለ ሰው መሆንን እንድፈልግ-አድርገውኛል።

"ከዚህ ግሩም-ከሆነ ጉዞ ሁላችንም ተምረን የምናተርፈው ነገር፣ ሁላችንም ከእያንዳንዳችን እንደምንማር ነው፣" ብለዋል ዘፍራን (Zefran)። "እራሴን ቲታን/Titan ብዬ ስጠራ - በታልቅ ኩራት ነው፤ ተማሪዎቻችን ያኮሩናል።" ሻባዝ (Shabazz) እንዳሉት፤

ፕሮጀክቱ አስተላላፊ የነበረ እና በዚህ “ነፍስን-ቀስቃስ በሆነ ተሞክሮ ውስጥ - ሚና መጫወት-መቻል” ክብር-ተሰምቷቸው እንደነበር-ገልጸዋል።

የ‘The Barbara Johns Youth’ ሽልማት ከK-12 የሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወይምእርምጃቸው፣ ውጤታማነታቸው እና እቅስቃሴአቸው በትምህርት ቤት ውስጥ ለሆኑ - የተማሪ ድርጅት፣ አዎንታዊ የቡድን-ውስጥ ግንኙነቶችን፣ ለሚኖሩ የተለያዩ ስብጥር አድናቆትን በመስጠት እና የራስን-ማንነት እና በራስ-መተማመን በሌሎች ላይ በማሳደግ ላይ የሚያበረታቱን ያቀርበ-ነበር።

## ለ‘PTAC Golden Apple’ ሽልማት - እጩዎችን መምረት ተጀምሯል




የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (PTAC)፤ የ2023 የ‘PTAC Golden Apple’ ሽልማት እጩዎችን - ማስገባት እንዲጀመር እየጠየቀ-ነው። የ‘PTAC Golden Apple’ ሽልማቶች - ለየአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ትምህርት-ሰጪዎች፤ - ከወላጆች እና ከእንክብካቤ-ሰጪዎች ጋር አጋርነትን በመፍጠር፣ የእያንዳንዱን ተማሪ ያለሁን-አቅም እውን-ለማድረግ - በቤተሰብ ተሳትፎ የላቀ-ደረጃን ላስመዘገቡት - ትምህርት-ሰጪዎች የሚሸልም-ነው።

“በእውነተኛነት የመኖሪያ-ቤት/ትምህርት ቤት አጋርነቶችን በአንድ-ላይ አቀናጅቶ መስራት የቻሉ አስተማሪዎችን ብርሃን-ማንፀባረቅ በላይ የሚያስደስተን ነገር የለም፤” ብለዋል የአሌክሳንድርያ የ‘PTAC’ ፕሬዚዳንት - ሚሲ እስታብሩክ (Missy Estabrook)። “ይህ ወሳኝ-የሆነ ትብብር፣ ወደ ተማሪው ውጤታማነት፣ ባህሪይ፣ በትምህርት-ገበታ መገኘት እና በራስ-መተማመን ላይ መሻሻልን-ለማምጣት የሚመራ-ነው። ትምህርት-ሰጪዎቻችንን ለሚያደርጉት-ሁሉ ለማመስገን በመጓጓት - እስከምናመሰግናቸው መጠበቅ-ያቅተናል።”

አርብ ኤፕሪል (April) 21 ቀን 2023 ላይ ሽልማት የሚሰጣቸውን፤ ምሳሌ-ሊሆኑ የሚችሉትን የPTAC Golden Apple እጩ አስተማሪን ለመምረጥ ጊዜ-ውሰዱ።

## የማርች (March) 30 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በማርች (March) 30 ቀን 2023 በሚደረገው ስብሰባው ላይ - የትምህርት ቤት ቦርድ፤ ከበጀት አድቫይዘሪ ኮሚቴው አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)ን፣ እና የስራ-መስክ እና ቴክኒካል ትምህርት (Career and Technical Education (CTE) - ፐርኪንስ የገንዘብ እርዳታን (Perkins Fund Grant)ን የሚያዳምጥ-ይሆናል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በማርች (March) 16 ቀን 2023 ላይ፣ የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ማርች (March) 16 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 28.23 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በማርች (March) 16 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ-ይመለከታል።